በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

***<u>ቦታ፦</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፲፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ

## ሱሰኝነት

- ብዙ ጊዜ ሱሰኝነትን በሰለጠነውም ሆነ ወደ ኋላ በቀሩ - በድሃውም ሆነ በባለጠጋው ኅብረተሰብ ዙሪያ የሠፈረ ‹‹አስፈሪ አውሬ›› ወይም ‹‹ጭራቅ›› አድርገን ስንገልጸው እንታያለን፡፡
- ሱሰኝነት ዘመናዊውን ኅብረተሰብ የከበበ ትልቅ በሽታ ነው፤ ሰብአዊና ተፈጥሮአዊ ሀብታችንን ተብትቦ በመያዝ አጥንትን የሚያስቀር ሀብትና አቅምን የሚያወድም ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ባለው አቅም ሰው ሁሉ ይዋጋዋል፡፡
- በተለይ ሱሰኛ አዳጊዎችና ወጣቶች ቁጥራቸው በሚያስደነግጥ መልኩ በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ የአገሪቱን መላ ሀብት ሊያሚጥጥ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ክስረት ወደ ጎን ትተን በአንዳንድ የምዕራብ አገሮች ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 75% የሚደርሱ ሱሰኞች ይገኛሉ፡፡
- በቅርብ ጊዜያት ውስጥ የምናያቸው የወንጀል ድርጊቶች መበራከትም ከሱሰኝነት ጋር የሚገናኝ ነው፡፡
- በአንዳንድ አገሮች ታላላቅ ፖለቲከኞችና ዳኞች በአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎች እጅ ሲገደሉ ይሰማል፡፡
- በርካታ ሱሰኞች ከአደንዛዥ ዕፅ የሚገኘውን ገቢ በመፈለግ የቤተሰብ አካላትን ሳይቀር ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ሲያጠቁ እየተመለከትን ነው፡፡ ‹‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፡፡›› ***ሆሴ 4፡6፡፡***
- ሱሰኝነትን ለመዋጋት ከፍ ባለ መጠን በዓለማችን እየተደረገ ካለው ጥረት ጎን ለጎን ላልቶ የሚታየው ቁጥጥር አደንዛዥ ዕፆችን በቀላሉ ለመገኘት አብቅቷቸዋል፡፡ ይህም ብዙ ሱሰኞችን የመመልከት አጋጣሚዎችን ፈጥሯል፡፡
- ቤተ ክርስቲያንና የሕዝብ ሽማግሌዎች ቁጥራቸው ይነስም ይብዛ ሱሰኞችን የመርዳት ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው፣ አንድም ሱሰኛ ቢሆን ከችግሩ ለመላቀቅ እገዛ ያስፈልገዋልና፡፡
- በሌላ አነጋገር የችግሩ መፍትሔ የሱሰኞች ቁጥር ማወቁ ወይም ያስከተለውን አደጋ መረዳቱ ላይ ሳይሆን ዕድሜና ሁኔታ ሳይለይ እያደረሰባቸው ያለውን አደጋና ያስከተለባቸውን ቀውስ ባለመረዳት ራሳቸውን ለዚህ ድርጊትና ሕይወት አሳልፈው የሰጡትን ተጎጂዎች መታደጉና ቀጣዩም ትውልድ በሚጠበቅበት አስፈላጊ አቅጣጫ ሲራመድ እንዲገኝ መረባረቡ ላይ ነው፡፡ ‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና፡፡›› ***ምሳ 1፡7፡፡***

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ

## ይመለከተኛል እንበል

- ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ የሕዝብ ሽማግሌዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የቤተሰብ ኃላፊዎች ሱሰኝነት በአሁኑ ወቅት እያስከተለ ያለውን ቀውስ ከልብ በመረዳት በአንድነት ሆነን ‹‹ሁላችንም ጉዳዩ ይመለከተናል፣ መፍትሔ ማፈላለግ አለብን፣ ለመፍትሔውም አብረን እንሥራን…›› ብለን መነሳሳት ይጠበቅብናል፡፡
- ይህም ማለት የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞችን ከመውቀስ አስቀድሞ እንደ ዜጋ፣ እንደ ክርስቲያን፣ እንደ ኦርቶዶክሳዊ መወቀስ ያለብኝ እኔ ራሴ ነኝ ማለት ይጠበቅብናል፡፡
- ምክንያቱም ሱሰኞች በርግጥም መራር ቅጣት የሚገባቸው ወንጀለኞች ሳይሆኑ ኅብረተሰቡ ባመጣባቸው ማኅበራዊ ደዌ ወይም ሕመም የሚማቅቁ በሽተኞች ናቸውና፡፡ እንዴት ልንል እንችል ይሆናል፤ ለዚህም የሚከተሉትን እንመልከት፡- ‹‹በተቀደሰውና ባልተቀደሰው መካከል ይለዩ ዘንድ ሕዝቤን ያስተምሩ፥ ንጹሕና ንጹሕ ባልሆነው መካከል ይለዩ ዘንድ ያሳዩአቸው።›› <u>*ሕዝ44፡23፡፡*</u>

1. <u>*ሱሰኝነት ከብቸኝነት ማምለጫ ስልት ሆኖ እያገለገለ ነውና*</u>

- የሱሰኝነት አንዱ ምንጭ ፍቅርን መነፈግና ከማኅበረሰቡ መገለል ወይም ብቸኝነት ነው፡፡ <u>*ማቴ 24፡12፡፡*</u>
- ምክንያቱም ሰው በእግዚአብሔር አምሳልና አርአያ የተፈጠረ እንደ መሆኑ እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ‹‹ፍቅር›› ይዞ ለመጋራትና ለማጋራት ይማስናል፡፡
- እያንዳንዱ ሰው መውደድና መወደድ ይፈልጋል… አንዳንድ ወንዶች ራሳቸውን አሳልፈው በማይሰጧቸው ወይም የእግዚአብሔርን ፍቅር በማያጋሯቸው ነገር ግን በሚያዝናኗቸው ወይም ጊዜን አብረዋቸው በሚያሳልፉ ሰዎች ተከበው ይውላሉ፡፡
- ራስን ለሌላው አሳልፎ መስጠት ደግሞ ታላላቅ መሪዎች ከሆኑ ካህናትና ምዕመናን የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህ ቢደረግ ሱሰኝነት ተቀባይነት ያጣ ነበር፡፡ ሱሰኛው ሰው በእውነተኛ ፍቅር ቢከበብ ወደ ሱሰንነት የመራው ብቸንነትና ባዶነት ባልተሰማው ነበር፡፡ <u>*ማቴ 10፡38፡፡*</u>

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ

## ይመለከተኛል እንበል...

2. ***<u>ሱሰኝነት ብቁ አይደለሁም ከማለት ይመነጫልና</u>***

- *አዲሱን ትውልድ የምናሳድግበት አቀጣጫ ትክክለኛ አለመሆኑ ልጆች ለራሳቸው ክብር እንዳይሰጡ አድርጓቸው በግልጽ ስለሚታይ እንደ ካህን፣ ወላጅና መምህር ሱሰኞችን ስንመለከታቸው ስለድካማቸው ኃላፊነት ይሰማናል፡፡*
- *በሰፊ ልቦና ሆኖ በፍቅርና በአክብሮት የሚያናግራቸው ከልጅነታቸውም ጀምሮ የልጅነት ዓለማቸውን ሐሳብ በመጋራት የብስለትን ጎዳና የሚያመለክታቸው ሰው ያገኙ ወጣቶች ሕይወታቸውን በክብር ሲይዙትና ሲጠብቁት እንደ ሰውም በብስለት ሲራመዱ ይገኛሉ፡፡*
- *አንድ ወላጅ ቤታቸው ሊባርኩ ለመጡት መንፈሳዊ አባት ስለልጃቸው አስቸጋሪነት በምሬት ያስረዳሉ፡፡ እኚህ አባትም አዳጊውን ‹‹እኔም በልጅነቴ እንዳንተ አስቸጋሪ ነበርኩ›› ብለው በሚማርክ ፈገግታ ሳም አደረጉት፤ አዳጊውም ከመቆጣት ይልቅ ከርሱ ጎን ስለቆሙ እጅግ ደስ አለው፡፡ መንፈሳዊው አባት እንደወጡም እንደወትሮው ጨዋታውን ቀጠለ፡፡ እናቱም እንደቀድሞው በወቀሳ ስታነጋግረው ‹‹መምህሩም በልጅነታቸው አስቸጋሪ ነበሩ፡፡›› ብሎ መለሰላት፡፡*
- *ካህናት፣ መሪዎች፣ ወይም ወላጆች ራሳችንን ከሌላ ዓለም የመጣን ወይም ከሌላ ተፈጥሮ የተገኘን ከእነርሱም የላቅን አድርገን ማቅረባችን ልጆቹ ፍጹም ተፈላጊነት እንደሌላቸውና ብቁ አይደለንም ወይም አንረባም አንጠቅምም ወደ ማለት ስለሚያደርሳቸው ጥንቃቄ ከማድረግ እንዳንዘናጋ፡፡*
- *አርአያነት ያላቸው መሪዎች ኩሩ ወይም ትምክህተኛ ፕሮፌሰር መስለው ከመቅረብ ይልቅ ባልንጀራ መስለው መቅረባቸው ዘወትር የሚጠበቅ ነው፡፡ ልጆችን በልጅነታቸው፣ ወጣቶቹንም በወጣትነታቸው ዓለም ልንቀርባቸውና ልናቀርባቸው ይገባናል፡፡* ‹‹አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል አምላካችሁ።›› ***<u>ኢሳ 40፡1፡፡</u>***

## ይመለከተኛል እንበል...

2. ***<u>ሱሰኝነት ብቁ አይደለሁም ከማለት ይመነጫልና...</u>***

- እግዚአብሔር ከሰው ሲነጋገር እንደ ወዳጅና ባልንጀራም በመሆን ነው፡፡ ስለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በኦሪት ***<u>ዘጸአት 32</u>*** የተጻፈልን የሚያስረዳን ይህንኑ ነው፡፡ ሙሴም እግዚአብሔርን ‹‹አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ፡፡›› ***<u>ዘጸ 32፡32፡፡</u>*** እኛም እንደዚሁ ለአዲሱ ትውልድ በግልጽ የመነጋገርን እድል ልንሰጠው ይገባናል፡፡
- ጭፍን ትእዛዞችን በማስተላለፍ ታዛዥነታቸውን የምንሻ ከሆን ባልጠበቅነው አቅጣጫ ሊሄዱ እንደሚችሉ እንወቅ፡፡
- የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የሆነ ልጅ ያለው አንድ ወላጅ በርሱና በልጁ መካከል በነበረ የተካረረ ንግግር መካከል በልጁ በጥፊ ስለተመታ መንፈሳዊ አባቱን ለማማከር ይሄዳል፡፡ አባትም ልጃቸውን ከቤት ለማባረር ስለወሰኑ መንፈሳዊ አባታቸው ይህን ለማድረግ የሚያስችለውን ፈጣን መንገድ እንዲያሳዩአቸው ጠየቁ፡፡
- መንፈሳዊውም አባት ልጁን ለማነጋገር ትኩረት ሰጥተው ቢቀርቡትም ገና በንዴት ውስጥ ስለነበር ባይፈልጋቸውም ‹‹አባትህ ስለ ግጭታችሁ ነግሮኛል እኔ ደግሞ ባንተ በኩል ያለውን ለመረዳት ለብቻህ እንድትነግረኝ ስለፈለግሁ መጥቻለሁና ልጄ ልታናግረኝ ፈቃድህ ነው?›› ብለው ጠየቁት፡፡ ልጅም ፈቃደኛ ሆኖ አስረዳቸው፡፡
- መንፈሳዊውም አባት የሁለቱንም ከሰሙ በኋላ በክርክራችሁ ጥፋቱ የሁለታችሁም ነበር ብለው ለአባትየው መለሱ፡፡ አባትየውም የንስሐ አባታቸው በነገሩአቸው ቢቆጡና ባይስማሙም የንስሐ አባታቸው ‹‹ጉዳዩን በራሴ መንገድ ወይም አቅጣጫ እንድዳኝና እንድፈታ ዕድል ይስጡኝ፤ በዚህም ሰላም ወደ ቤታችሁ ይመለሳል፡፡›› ብለው ሲጠይቁ ሲፈቅዱላቸው ‹‹የኔ አቀራረብ ልጅዎ አንድ ሰው ከጎኑ ያለ ሆኖ እንዲሰማው ያደረገው መሆኑን፣ የአባትነትዎንም ድርሻ ለመረዳት እንዳስቻለው›› አስረዱ፡፡ ልጁን በአባቱ ፊት አቅርበው ማሳፈር ባይፈልጉም ሁኔታዎችን እንዲገነዝብና ስህተቱን ለመረዳት ለሚችልበት ደረጃ አብቅተው ኃላፊነታቸውን ተወጥተው ችግራቸውን ፈቱላቸው፡፡

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ

## ይመለከተኛል እንበል…

2. ***<u>ሱሰኝነት ብቁ አይደለሁም ከማለት ይመነጫልና…</u>***

- በርግጥም እውነተኛ መሪ ልጁን በልጅነቱ ዓለም፣ ወጣቱን በወጣትነቱ ዓለም ሳያበሳጭና ሳያስጨንቅ በብስለትና በጥበብ የሚቀርበውና የሚያቀርበው ነው፡፡ እንዲህም በማድረግ ካቀረብነው አዲሱ ትውልድ አላስፈልግም ከሚል ወደ ሱሰኝነትም ከሚመራ ስሜት ተላቆ ኃላፊነቱን የሚወጣ ይሆናል፡፡

3. ***<u>ሱሰኝነት ከአመጸኝነት የተነሳ ይከሰታልና</u>***

- ሱሰንነት በዓለም፣ በአካባቢያችን ወይም በቤተሰባችን ውስጥ ከሚታየው አመጸኝነት የሚመነጭ ሊሆን ይችላል፡፡
- ሚዲያዎች በርግጥም ውስጣዊ መረጋጋትን በማሳጣት አመጸኝነትን የሚቀሰቅሱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ይሁን እንጂ በቤተሰብ ውስጥ ያለ ነውጠኝነት በሚዲያ ካለው የላቀ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡
- በወንድምና እህት ወይም በዘመድ ላይ ወይም በወላጆች ላይ የሚታየው ነውጠኝነት ቤተሰባዊ ሰላምን በምሬትና ነውጠኝነት ስለሚተካ ይኸው ድርጊት በቀላሉ የሚወረስና ከዚህም ለመሸሽ የሚሞክሩትን ለሱሰኝነት የሚያጋልጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ***<u>ዘፍጥ 19፡1-ፍም፡፡</u>***

4. ***<u>ሱሰኝነት ከተሳሳተ አመለካከትና እምነት ይመነጫል</u>***

- በቀጥታም ይሁን በተዘዋውወሪ የተሳሳተው አስተሳሰብ ምንጮች ወይም የተሳሳተውን አስተሳሰብ አውቀን ማስተካከያውን ስላላፈላለግን ተሳታፊ ስለሆን ለሱሰኞች ሱሰኝነት ተጠያቂዎች ነን፡፡ ከተሳሳቱትም አመለካከቶች፡- <u>ስለ ነጻነት ያለን የተሳሳተ አስተሳሰብ አንዱ ነው</u>
- የነጻነትን ትርጉም ‹‹ከልልነትና ግድየለሽነት›› ጋር ቀላቅሎ መመልከት በስፋት ይታያል፤ በዚህም የተነሳ ነጻነት ስለሌሎች ክብርና ፍላጎት ትኩረት በመንፈግ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ የፈለግነውን ማድረግ ተደርጎ ተዋስዷል፡፡
- የተበላሸ ሰው ችግር ከገጠመው በራሱ ሀሳብ ገምግሞ በባልጀሮቹ መጠለያ ተጠልሎ ባልንጀሮቹ ሱሰኝነትን ደስታና መዝናናት ነው አስመስለው የሚሰጡትን ምክር የሚቀበል ይሆናል፡፡ ***<u>ፊል 3፡19፡፡</u>***

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org